# የተሳካ ውጤት ከምንም በላይ ነው
## የወላጆች መምሪያ



የሜሪላድ እቅድ ከቅድመ-አፀደ-ሕጻናት-12 እትም

በጃንዋሪ 2004 እንደገና ተሻሻለ

Amharic

## የተሳካ ውጤት ከምንም በላይ ነው፤ የወላጆች መምሪያ


# የሜሪላንድ ክፍለ-ግዛት
# የትምህርት ቦርድ

Edward L. Root
*ፕሬዚደንት*

Jo Ann T. Bell
*ምክትል ፕሬዚደንት*

Dunbar Brooks
Calvin D. Disney
**የተከበሩ** Clarence A. Hawkins
Walter S. Levin
Karabelle Pizzigati
Maria C. Torres-Queral
John L. Wisthoff
**ክፍት ቦታ**
Christopher J. Caniglia (*አባል ተማሪ*)

Nancy S. Grasmick
*ግዛታዊ የትምህርት ቤቶች የበላይ ጠባቂ ቦርድ*
*ዋና ጸሃፊ-የንብረት ክፍል*



MARYLAND STATE DEPARTMENT OF EDUCATION
**የአካዳሚያዊ ፖሊሲ ቢሮ**
Ronald Peiffer, **ምክትል የበላይ ተቆጣጣሪ**
200 West Baltimore Street • Baltimore, Maryland 21201-2595
**ስልክ**: 410-767-0600/888-246-0016 • **ፋክስ**: 410-333-2275
www.marylandpublicschools.org


**የሜሪላንድ ክፍለ-ግዛት የትምህርት ክፍል፣ ለቅጥር ሥራም ሆነ ፕሮግራምን ለመጠቀም፣ በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በትውልድ ወይም ብሄር፣ በሃይማኖት፣ ወይም በእካለ-ጎደሎነት ላይ የተመሰረተ ልዩነት አያደግም:: የዲፓርትሜንቱን ፖሊሲ በተመለከተ ጠይቆ ለመረዳት፣ የዕኩልነት ዋስትና አስከባሪ ቅርንጫፍን በሚከተሉት አድራሻዎች ያነጋግሩ::**


Equity Assurance and Compliance Branch
Maryland State Department of Education
200 West Baltimore Street
Baltimore, MD 21201-2595
ስልክ: 410-767-0433 TTY/TDD 410-333-6442
ፋክስ: 410-767-0431

# ማውጫ


**በሜሪላንድ የህዝብ ትምህርት ላይ የተደረጉ ለውጦች** 2

**የስራ ውጤት ከምንም በላይ ነው** 4

**ከፍተኛ ግምት** 6

**ሥርዓተ-ትምህርት (ካሪኩለም)** 8

**እድገትን መለካት (መመዘን)** 10

የሜሪላንድ የትምህርት ቤት ግምገማ 10

የሜሪላንድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግምገማ 16

**የተለየ ትኩረት የሚያስፈልጋቸውን እና/ወይም ዝቅተኛ የእንግሊዝኛ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ስለመገምገም** 21

**ኃላፊነት (ተጠያቂነት)** 22

**የቤተሰብ ተሳትፎ** 24

**የስራ ውጤትን ስለማበረታታት** 26


**ለበለጠ ኢንፎርሜሽን** 28

# በሜሪላንድ የህዝብ ትምህርት ላይ የተደረጉ ለውጦች

እንደወላጅነተዎ ለልጆቸዎ ይበልጥ የላቀውን ጥሩውን ነገር ሁሉ ይፈልጋሉ። ያም ለወደፊቱ ጥሩ ህይዎታቸው የሚያዘጋጃቸውንና በደረጃ አንደኛ የሆነውን የትምህርት አይነት ይጨምራል። የሜሪላንድ ክፍለ-ግዛትም እንደዚሁ ሕጻናት በጣም ጥሩ የሆነውን ነገር እንዲያገኙ ይፈልጋል።

የእያንዳንዱን ተማሪ የስራ ውጤት ለማሳደግ፣ ሜሪላንድ፥ ማስተማርን፣ ግምገማን፣ ደህንነትን፣ እና በትምህርት ቤቶች የቤተሰብ ተሳትፎን ያካተተ ውጤት ከምንም በላይ ነው የሚል፣ ለህዝብ ትምህርት ቤቶች የሚሆን ግብን የነጣጠረ እቅድ አዘጋጅቷል። ውጤት ከምንም በላይ ነው የሚለው መርህ ለተሻሉ ትምህርት ቤቶች ምልከታ የተቋቋመ ራዕያዊ ግብረ-ሃይል የተባለው ክፍል ክንዋኔ ላይ የተመሰረተ ሲሆን፣ እንደዚሁም ማንም ልጅ ወደኋላ እንዳይቀር የሚለውን የ2001 ድንጋጌን እና የህዝብ ትምህርት ቤቶችን ወደላቀ ደረጃ የሚያሸጋግር ድልድይ ድንጋጌ የሚሉትን ድንጋጌዎችም ያካትታል።

ለተሻሉ ትምህርት ቤቶች ራዕይ የተሰየመው ግብረ-ሃይል የሜሪላንድን የትምህርት ቤት ሁኔታ ለማሻሻል ጥረት ያደረገ፣ እንደዚሁም ለማሻሻል የሚረዱ ጠቃሚ ምክሮችን ሲሰጥ የቆየ፣ ከወላጆች፣ ከአስተማሪዎች፣ ከአስተዳዳሪዎች፣ ከኮሌጅ ፕሮፌሰሮች፣ ከፖሊሲ አውጪዎች፣ እና ከብሄራዊ የትምህርት ጠበብቶች የተውጣጣ ቡድን ነበር። የግዛቲቱ የትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ የሆኑት Nancy S. Grasmick፣ በሜሪላንድ፣ የተሻሻለና አዲስ የትምህርት ቤት ዕቅድ እንዲያቀዱላቸው በማለት እነዚህን የፓነል አባላት አሰባስበዋል። የነሱ ጠቃሚ አስተያየቶችና ምክሮችም፣ ውጤት ከምንም በላይ ነው ለተባለው መርህ የጀርባ አጥንት ናቸው።



ማንም ልጅ ወደኋላ እንዳይቀር የሚለው ድንጋጌ በዩናይትድ ስቴትስ ኮንግሬስ አማካኛነት ተላልፎ፣ በጃኑዋሪ 8, 2002 ዓ.ም በህግነት የጸደቀ ነው። ይህ ህግ የሀገሪቱ የተለያዩ ክፍለ-ግዛቶች የትምህርት ቤት መመዘኛ

መስፈርቶችን እንዲያዳብሩና የተማሪዎቻቸውም እድገት በዚሁ መስፈርት መሰረት እንዲራመዱ ማድረግን፤ የ“ሪፖርት ካርዶችንም” በየትምህርት ቤቶቹ እንዲያሳትሙ፤ መምህራንም በሚገባና በላቀ ሁኔት የሰለጠኑ መሆናቸውን እንዲያረጋግጡ፤ እንደዚሁም ትምህርት ቤቶች በደህና ሁኔታ ላይ ሳይሆኑ ሲቀሩ ወይም በቂና አስተማማኝ የአካዳሚያዊ እድገት የማያሳዩ ሆነው ሲገኙ አፋጣኝ እርምጃ መውስድ ያለባቸው መሆኑን ይደነግጋል። ሜሪላንድ እነዚህን ነገሮች ለብዙ ዓመታት ስትሰራ ቆይታለች። ይሁንና፤ እዲሱ ህግ፤ ለሜሪላንድ፤ ሁኔታዎችን ለማሻሻል ብሄራዊ መመሪያና የቁርጠኛ ቀን ሃሳብ ሰጥቷታል።

የህዝብ ትምህርት ቤቶችን ወደላቀ ደረጃ የሚያሸጋግር ድልድይ ድንጋጌ የተላለፈው በሜሪላንድ ጠቅላላ ጉባዔ በጸደይ 2002 ዓ.ም ነበር። ድንጋጌው ለህዝብ ትምህርት ቤቶች የሚመደበው ገንዘብ እንዲጨምር እድረጓል፤ ልዩ የትምህርት አሰጣጥ ትኩረት ለሚያሻቸው ተማሪዎች የሚውለው የገንዘብ መጠንም እንዲጨምር መመሪያ ሰጥቷል፤ እንደዚሁም የትምህርት ቤት ስርዓቶች የተመደበላቸውን ገንዘብ እንዴት ማዋል እንዳለባቸው በሚመለከት ሰፊ የሚያዝናና እድል ሰጥቷል። ለነዚህ ገንዘባዊ ምደባዎች ምላሽም እያንዳንዱ የትምህርት ሥርዓት ለሁሉም ተማሪዎቻቸው ጥሩ ውጤትን ለማስመዝገብ የሚያበቃ እቅድ ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል። እንደዚሁም ደግሞ የትምህርት ሥርዓቶቹ፤ ሙሉ ቀን አገልግሎት የሚሰጥ የመዋዕለ-ሕጻናት መርሀ-ግብር፤ ለሁሉም ሕጻናት ማሰናዳት፤ ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ቤተሰቦች ለሚመጡ የቅድመ-መዋዕለ-ሕጻናት ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል።




**የሜሪላንድ ክፍለ-ግዛትም እጅግ በጣም ጥሩው ነገር ሁሉ ለሕጻናት እንዲሆን ይፈልጋል።**


# የተሳካ ውጤት ከምንም በላይ ነው

ውጤት ከምንም በላይ ነው የሚለው መርህ፤ ለሜሪላንድ የህዝብ ትምህርት አምስት ቀላል፤ ግን ፈታኛ ግቦችን ያስቀምጣል።

**ግብ 1: *እያንዳንዱ ተማሪ ውጠቱ ይበልጥ ይሻሻላል (ያድጋል)።*** የማንኛውም የትምህርት እቅድ ወይም ፖሊሲ፤ የተማሪን ውጤት የበለጠ ለማሻሻል ነው። በዚህ ላይ ሜሪላንድን የተለየ የሚያደርገው ግን ለእያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የመስጠቱ ጉዳይ ነው። ከተለያዩ ጎሳዎችና ማህበረሰቦች፤ የቤተሰብ የገቢ መጠን፤ የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች፤ በሚመጡ፤ ወይም የአካል ጉድለት ባለባቸውና በጤነኞች መካከል የሚፈጠር  የትምህርት ክንዋኔ ክፍተትን ወይም ሰፊ ልዩነትን ለማስወገድ ሜሪላንድ ቁርጠኛ አቋም አለው። ሁሉም ተማሪዎች ውጤት ማግኘት መቻላቸውን ለማረጋገጥ፤ ትምህርት ቤቶች በጎሳ/በብሄረሰብ፤ በጾታ፤ በአካለ-ጎደሎነት፤ በድህነት ደረጃ፤ በስደተኛነት ደረጃ፤ ወይም በተወሰነ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ላይ ልዩነት ሳያደርጉ በሁሉም ተማሪዎች ዘንድ አመርቂ የአካዳሚያዊ እድገት ማሳየት ይጠበቅባቸዋል። ቀጥሎ የተመለከቱት ግቦች የዚህን ግብ ስኬታማነት ይደግፋሉ።

**ግብ 2: *ሥርዓተ-ትምህርት፤ የትምህርት እሰጣጥ ዘይቤ፤ እና ግምገማ የተቀናጁና ለመረዳትም የቀለሉ ቢሆኑ ይመረጣል።.*** ሥርዓተ-ትምህርት፤ የትምህርት አስጣጥ ዘይቤ እና ግምገማ፤ የትምህርት መሰረታዊ ቁሶች ናቸው። በሦሥቱ መካከል የሚኖር የተጣጣመ ትስስር ወይም ቅንጅት ወሳኛ ነው።  ሜሪላንድ፤ መምህራን በእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት፤ በእያንዳንዱ ግብ ዙሪያ ምን ዓይነት ይዘትና ሙያ ለተማሪዎች ማስተማር እንደሚገባቸው ግልጽ የሚያደርግ አዲስ ሥርዓተ-ትምህርት በማዘጋጀት ላይ ይገኛል። የሜሪላንድ ግምገማም፤ ተማሪዎች በሥርዓተ-ትምህርቱ አኳያ የተቀረጹትን የሙያና የይዘት አቅርቦቶችን ምን ያክል በአግባቡ እንደተማሩ ይለካል። የግምገማ ውጤቶችም መምህራን የተማሪዎቻቸውን ጠንካራና ደካማ ጎኖች እንዲለዩና የትምህርት አቀራረብ ዘይቤያቸውንም በዚሁ አኳያ እንዲያሻሽሉ ይረዳቸዋል። የግምገማ ውጤቶች እንደዚሁም ወላጆች ስለልጆቻቸው አካዳሚያዊ ክንዋኔ ግልጽ የሆነ ስዕል እንዲኖራቸው ይረዳቸዋል።

**ግብ 3: *የተማሪዎች ውጤትን ለማሻሻል፤ ሁሉም አስተማሪዎች በቂ ሙያዊ ችሎታ ሊኖራቸው ይገባል።*** ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት እንዲያገኙ ከተፈለገ፤ ሥርዓተ-ትምህርቱን እናም እንዴትስ ማስተማር እንዳለባቸው በሚገባ የሚያቁ እስተማሪዎች ያስፈልጓቸዋል። ሜሪላንድ ለክፍል መምህርነት ምርጥ የሆኑ ዕጩዎችን ማሰልጠንና በሙያውም ላይ ተረጋግተው እንዲቆዩ የሚያደርግ በቂ ምክንያታዊ ዋስትና መስጠት ይኖርበታል። አዳድስ እስተማሪዎች፤ እገዛ፤ ምክርና ሥልጠና ያስፈልጋቸዋል፤ ሁሉም አስተማሪዎች



ተከታታይ ስልጠና እና የሚያቀርቧቸውን ትምህርቶች የሚያቅዱበትና የሚያዘጋጁበት በቂ ጊዜ ያስፈልጋቸዋል፡፡ እንደዚሁም ደግሞ፤ ሁሉም ትምህርት ቤቶች፤ በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ ኃላፊ (ርዕሰ-መምህር) አመራር ያስፈልጋቸዋል፡፡

ግብ 4: ሁሉም ትምህርት ቤቶች ሰላማዊ፤ ከሱስ-አስመጪ ዕጾች የጸዱ፤ እና ለመማር የሚጋብዙ እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡ ሁሉም ተማሪዎች ውጤታማ ሊሆኑ በሚችሉበት ትምህርት ቤት ገብተው የመማር መብት አላቸርው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ትምህርት ቤቶች፤ ለመማር የሚጋብዝ ሰላማዊ፤ ጤናማ የትምህርት አየር መፍጠር ይኖርባቸዋል ማለት ነው፡፡ በትምህርት ቤት ለሚነሳ ብጥብጥ ወይም የሽብር ሁኔታ፤ የሜሪላንድ ትምህርት ቤቶች ለደህንነት ክፍተኛውን ቅድሚያ ይሰጣሉ፡፡ ሁሉም የሜሪላንድ ትምህርት ቤቶች የደህንነትን እስተማማኝነት ለመጨመርና ወከባንና የማንገላታት (የማገጣበር) ሁኔታን ለመቀነስ ይቻል ዘንድ፤ የተነደፈውን የመንግስት ደንብ በሚገባ መከተል ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህም በላይ፤ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት በአካባቢያዊው የትምህርተ-ስርዓት ዕቅድ ላይ የተመሰረተ የየራሱ የደህንነት አጠባበቅ ዕቅድና የስነ-ምግባር መመሪያ ይኖረዋል፡፡ የትምህርት ቤቱን ስነ-ስርዓትና የደህንነት ፖሊሲውን በተመለከተ ለመወያየት የልጅዎን ትምህርት ቤት ያነጋግሩ፡፡

ግብ 5: ወላጆችና ህጋዊ ሞግዚቶቹ በትምህርት ጉዳይ ላይ ይሳተፋሉ፡፡ እንደወላጅ ወይም እንደህጋዊ ሞግዚት (አስዳጊ)፤ ወላጆቻቸው በትምህርት ቤት ጉዳይ የሚሳተፉ ልጆች ከፍተኛ ውጤት እንደሚያገኙ፤ በባህሪያቸውም ጥሩ እንደሚሆኑ፤ ከፍተኛ ሁለተኛ ደርጃንም አልፈው ትምህርታቸውን ለመቀጠል ዕድላቸው ሰፊ መሆኑን፤ ምናልባት እርሰዎም የሚያውቁት ይሆናል፡፡ በትምህርት ጉዳይ የውላጆች ተሳትፎ የመምህራኑንም ሞራል ይበልጥ ያነቃቃል፤ እንደዚሁም ቤተሰቦችንና ማህበረሰቦችን የበለጠ ያቀራርባል፡፡ ዘውትር፤ በትምህርት ቤትና በቤት መካከል የሚደረግ ባለ-ሁለት-ጎንዮሽ ግንኙነት (ንግግር)፤ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የወላጅ ተሳትፎን ለማበረታታት፤ ትምህርት ቤቶች ዘወትር፤ በግልጽ፤ እና ግሩም ድንቅ በሆነ አነቃቂና አበረታች ሁኔታ ከቤተሰቦች ጋር መገናኘትና መነጋገር፤ እንደዚሁም ቤተሰቦች የልጆቻቸውን ሁኔታዎች ሊነኩ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ የውሳኔ ሃሳባቸውን እንዲያቀርቡ ወላጆችን መጠየቅ ይኖርባቸዋል፡፡

# ከፍተኛ ግምቶች

ሁሉም ልጆች እኩል የውጤታማነት ዕድል እንዲኖራቸው ማድረግ ከተፈለገ፤ ትምህርት ቤቶች ለሁሉም ተማሪዎች ከፍተኛውን ግምት ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል። ይህን ለማድረግም፤ ሜሪላንድ ለከፍተኛ ግምት የሚያበረታታቸውና ትምህርት ቤቶችም ለሁሉም ተማሪዎች የሚሆን መሻሻል እንዲያደርጉ የሚርዱ ናቸው የሚላቸውን እንዲያው ጥቂት መንገዶችም እነሆ ከዚህ ቀጠሎ ተመልክተዋል:

- ሜሪላንድ የፈቃደኛ ክፍለ-ግዛቶች ሥርዓተ-ትምህርት ተማሪዎች በእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነትና የክፍል ደረጃ ምን መማር እንዳለባቸው ለአስተማሪዎችና ለወላጆች ግልጽ ያደርጋል።

- የሜሪላንድ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎችን የንባብና የሂሳብ ችሎታ፤ እንደዚሁም በክፍል ውስጥ አዘውትሮ የመገኘት ወይም የምረቃ መጠንን ለማሻሻል የሚረዱ ዓመታዊ ግቦች አሏቸው። ትምህርት ቤቶች በቂ ዓመታዊ እድገትን ለማግኘት ይቻላቸው ዘንድ፤ ግቦቻቸውን በሁሉም ተማሪዎቻቸው ንዑስ ቡድኖች አኳያ ዕውን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ሥምንት ንዑሳን ቡድኖች አሉ፥ አምስት የጎሳ/የማህበረሰብ ንዑስ ቡድኖች፤ የአካል ጉድለት ያለባቸው ተማሪዎች፤ ውሱን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች ንዑስ ቡድን፤ ነጻ ወይም የባለ ቅናሽ ዋጋ ምግብ የሚያገኙ ተማሪዎች (የድህነት ደረጃን አመልካች ነው)።

- በቂ ዓመታዊ ዕድገት የማያደርጉ ትምህርት ቤቶች በክፍለ-ግዛቲቱ ውስጥ ያሉ ትምህርት ቤቶች ከሚጠበቅባቸው የዕድገትና መሻሻል ሂደት አኳያ፤ ለሁለት ዓመታት ያክል ሁኔታቸው ታውቆና እየተገመገሙ ይቆያሉ። ለበለጠ ኢንፎርሜሽን፤ ኃላፊነት (ተጠያቂነት) እና የክፍለ-ግዛቲቱ የትምህርት ቤቶች የዕድገትና መሻሻል ሂደት የሚለውን በገጽ 22 ላይ ይመልከቱ።



- የትምህርት ቤት የስራ አፈጻጸም በየዓመቱ በዓመታዊ የሪፖርት ካርድ ላይ (የሜሪላንድ የትምህርት ቤት የስራ አፈጻጸም ሪፖርት) ሪፖርት ስለሚደረግ ወላጆችና ማህበረሰቦች (ኮሚዩኒቲዎች) ትምህርት ቤቶቻቸው እንደት እየሰሩ እንደሆኑ ለማወቅ ይቻላቸዋል። የልጅዎ ትምህርት ቤት የዚህን ሪፖርት ቅጂ ይሰጠዎታል። እንደዚሁም ኢንፎርሜሽኑን በደረ-ገጽ www.mdreportcard.org ላይ ማግኘት ይቻላል።



- እያንዳንዱ ትምህርት ቤት የተማሪን የመማር ሁኔታ ለማሻሻልና ለማሳደግ የሚጥር የትምህርት ቤት የዕድገት ቡድን አለው። እነዚህ ቡድኖችም ከመምህራን፣ ከወላጆች፣ እና ከኮሚዩኒቲ አባላት የተውጣጡ የትምህርት ቤት የስራ አፈጻጸምን መረጃ የሚያጠኑና የትምህርት አሰጣጡም በምን ሁኔታ መሻሻል እንዳለብት የሚወስኑ ናቸው።

- በሁሉም የተማሪ ቡድኖች ዘንድ ጠንካራ የትምህርት አፈጻጸም ዕድገትና መሻሻልን ላሳዩ ትምህርት ቤቶች የገንዘብ ሽልማትና የሕዝብ ዕውቅና ሊሰጥ ይችላል።

- የግዛቲቱ የቤተሰብ ተሳትፎ ፖሊሲ የትምህርት ቤት መሪዎች፣ ቤተሰቦች፣ እናም ማህበረሰቦች በጋራ ትብብር እንዲሰሩና ስለልጆች የትምህርት ጉዳይ የጋራ ኃላፊነትን እንዲወስዱ ያበረታታል።

ትምህርት ቤቶች ውጤት ከምንም በላይ ነው የሚለውን ግባቸውን ይመቱ ዘንድ ሜሪላንድ እንዴት እየረዳ እንደሆነ የሚቀጥሉት ገጾች ይበልጥ ያብራራሉ። እንደዚሁም በልጅዎ የትምህርት ጉዳይ እንዴት እንደሚሳተፉ የሚገልጹ አስተያየቶችና ምክሮችም አሉ። *ውጤት ከምንም በላይ ነው የሚለውን የወላጆች መምሪያን* ካነበቡ በኋላ፣ የተማሪ የትምህርት አፈጻጸምን ለማሳደግ ምን እየተደረገ እንደሆነና እርሰዎም የበኩለዎን እርዳታ ለማድረግ ምን ማድረግ እንደሚችሉ ከልጅዎ መምህር ወይም ርዕሰ-መምህር ጋር ሊነጋገሩ ይችላሉ።

# ሥርዓተ-ትምህርት (ካሪኩለም)

ሚሪላንድ በፈቃደኛነት ላይ የተመሰረተ ግዛት አቀፍ ሥርዓተ-ትምህርት ለማዘጋጀት ስትሰራ ቆይታለች።

## ሥርዓተ-ትምህርት (ካሪኩለም) ምንድን ነው?

ሥርዓተ-ትምህርት (ካሪኩለም) ተማሪዎች በእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነትና የክፍል ደረጃ አኳያ ምን መማር እንዳለባቸው የሚገልጽ ሰንድ ነው። መምህራንም የትምህርት ዝግጅቶቻቸውን እንዴት እንደሚያቅዱ የሚያመላክት ሲሆን የትምህርት አቀራረብን ይበልጥ ላማሻሻልም የሚረዳ ዋነኛው ክፍል ነው። በተለምዶ፤ 24ቱም የሜሪላንድ አካባቢያዊ የትምህርት ስርዓቶች፤ ተማሪዎች በአንደኛ ደረጃ፣ በመካከለኛ ክፍል፣ እና በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ምን ምን መማር እንደሚገባቸው ከሚያብራራው የሜሪላንድ የትምህርት ይዘት መለኪያ ጋር በሚጣጣም መልኩ የየራሳቸውን ሥርዓተ-ትምህርት ይቀርጻሉ።

## የክፍለ-ግዛት ሥርዓተ ትምህርት መቅረጽ ለምን አስፈለገ?

ምንና መቸ ስለማስተማር በየትምህርት ሥርዓቶች መካከል ልዩነቶች አሉ። ምን ማስተማር እንደሚገባ ለመምህራን ግልጽ እንዲሆንላቸውና እንዲረዱትም ለማገዝ፤ ሜሪላንድ፣ በጣም ግልጽና የተሟላ ዝርዝርን ያካተተ በፈቃደኛት ላይ የተመሰረተ ክፍለ-ግዛት-አቀፍ ሥርዓተ-ትምህርትን እያዘጋጀች ነው።

## የክፍለ-ግዛቱ ሥርዓተ-ትምህርት የግዴታ ሳይሆን ለምን በፈቃደኛነት ይሆናል?

ሥርዓተ-ትምህርትን የሚመለከት ውሳኔ የሚወስነው በአካባቢው የትምህርት ቦርድ እንጂ በክፍለ-ግዛቷ መንግስት አይደለም። አዲሱ የሜሪላንድ ሥርዓተ-ትምህርት ሁሉም የትምህርት ሥርዓቶች እንደራሳቸው ካሪኩለም አድርገው እንዲጠቀሙበት ወይም ከራሳቸው ሥርዓተ-ትምህርት ጋር ፀማጣጣም እንዲገለገሉበት ዝግጁ ይሆናል። የክፍለ-ግዛቱን ሥርዓተ-ትምህርት እንዳለ ተቀብሎ በስራ ላይ ማዋል ግዴታ አይደለም።

## በፈቃደኛነት ላይ የተመሰረተው የክፍለ-ግዛት ሥሮዓተ-ትምህርት ከሜሪላንድ የትምህርት ይዘት ደረጃ እንዴት ይለያል?

የሜሪላንድ የትምህርት ይዘት መለኪያ ደረጃዎች እንደሚገልጸው፤ ተማሪዎች እጅግ ቢያንስ በአንደኛ ደረጃ፣ በመካከለኛ ክፍል፣ እና በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ መማር ይኖርባቸዋል። ሁሉም የክፍለ-ግዛቱ የትምህርት ግምገማዎች በሜሪላንድ የትምህርት ይዘት ደረጃዎች ላይ የተመሰረቱ መሆን ይኖርባቸዋል። ነገር ግን፤ የሜሪላንድ የትምህርት ይዘት ደረጃ በእያንዳንዱ ክፍል ምንን ማስተማር እንደሚገባ አይገልጽም። የሜሪላንድ የፈቃደኛነት ሥርዓተ-ትምህርት ግን ከይዘት ደረጃዎች የበለጠ ዝርዝር ጉዳዮችን ያካትታል። ሥርዓተ-ትምህርቱ ታዲያ፤ በእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት አኳያና በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ምን

ማስተማር እንደሚገባ ያብራራል (ንባብ/የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበብ፤ ሂሳብ፤ ሳይንስ፤ ሕብረት ትምህርት፤ ስነ-ጥበብ፤ ጤና፤ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት፤ እና የውጪ ቋንቋዎች)።

## ሥርዓተ-ትምህርቱ ምን ሊመስል ይችላል?

የሜሪላንድ የፈቃደኛነት ሥርዓተ-ትምህርት ሦሥት የዝርዝር ደረጃዎች ይኖሩታል: የትምህርት ይዘት ደርጃ መለኪያ፤ አመልካቾች፤ እና ዓላማዎች። አመልካቾች ከክፍለ-ግዛቱ የይዘት ደረጃዎች አኳያ ምን ምን መገምገም እንዳለበት ይገልጻሉ። ዓላማዎች እያንዳንዱ ተማሪ በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ሊማር የሚገባውን የትምህርት ይዘት ወይም የሙያ ክህሎቶችን ይዘረዝራሉ። ሦሥቱ የዝርዝር ደረጃዎች መምህራኑ የትምህርት ዝግጅቶቻቸውንና ለተማሪዎቻቸው የሚሰጧቸውን የቤት ስራዎች በአግባቡ እንዲያቅዱ ይረዷቸዋል። ከዚህ በታች የተመለከተው ሥርዓተ-ትምህርቱ ምን ሊመስል እንደሚችል በምሳሌነት ለማሳየት የተቀነጨበ ትንሽ ክፍል ነው። ይህ ምሳሌም የሚያሳየው ተማሪዎች በስድስተኛ ክፍል ደረጃ ሊማሯቸው ከሚገቡት በርካታ የሂሳብ ችሎታዎች መካከል  አንዱ የሆነውን ነው: የስሌት እኩልዮሽን እና እኩል የማይሆኑ ስሌቶችን።

### የ 6ኛ ክፍል ሂሳብ

- የይዘት ደረጃ መለኪያ: የአልጀብራ፤ የፓተርኖች ወይም የፋንክሽኖች እውቀት። ተማሪዎች ፓተርናዊ ወይም ፋንክሽናዊ ስሌታዊ መስተግብሮችን በመጠቀም በአልጀብራዊ ስልት ስሌቶችን በማስቀመጥ፤ በሞደል በመቅረጽ፤ በመተንተን፤ ሂሳባዊ ወይም የተጨባጩን ዓለም ፕሮብሌሞች ለመፍታት ይችላሉ።
  - የእመልካች መግለጫ: መለየት፤ መጻፍ፤ ማቃለል፤ እናም እኩል የሚሆኑና እኩል የማይሆኑ ስሌቶችን መጠቀም።

    ዓላማ:

    - ስሌታዊ መስተግብሮችን ለማስቀመጥ እኩዮችንና እኩያ ያልሆኑ ስሌቶችን መጻፍ።
    - የማይታወቀውን ልይቶ በሊኒየለር ኢኩዌሽን ላይ ማሳየት።

## ሥርዓተ-ትምህርቱ መቸ ይጠናቀቃል?

በፈቃድኛነት የተዘጋጀው የግዛቲቱ ሥርዓተ-ትምህርት፤ በንባብ/የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበብ፤ በሂሳብ፤ በሳይንስ፤ እና በሕብረት ትምህርት፤ ከቅድመ መዋዕለ-ሕጻናት ጀምሮ እስከ 8ኛ ባሉት ክፍሎች፤ እንደዚሁም በንባብ በ10ኛ ክፍል ደረጃ እየተሞከረ ነው። መንግስትና የአካባቢ የትምህርት ባለሙያዎች በአሁኑ ወቅት የሜሪላንድን የፈቃደኛነት ሥርዓተ-ትምህርት ለውጪ ቋንቋዎች፤ ለሥነ-ጥበበ፤ ለጤና፤ እና ለአካል ማጎመሻ ትምህርት፤ እንደዚሁም በክፍለ-ግዛቲቱ በሚሸፈኑ የትምህርት ዓይነቶች ላይ ለሚዘጋጁ የክፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ቴስቶች ፥ ለአልጀብራ/ዳታ ትንተና፤ ለጂዖሜትሪ፤ ለእንግሊዝኛ I፤ ለስነ-መንግስት፤ እና ለባዮሎጂ በሚስማማ መልኩ እያዘጋጁት ነው፤፤ በፈቃደኛነት ላይ ተምስርቶ እየተዘጋጀ ስላለው ሥርዓተ-ትምህርት ወቅታዊ ደረጃ በይበልጥ ለመረዳት፤ የሜሪላንድ ክፍለ-ግዛት የትምህርት ክፍልን ድረ-ገጽ www.marylandpublicschools.org ይመልከቱ።

# እድገትን ሥለመለካት

ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የቱን ያክል በደንብ እየተማሩ እንደሆነ ለመለካትና ለማዎቅ፤ ቴስቶችን ይሰጣሉ። የቴስት ውጤቶችም ለርዕሰ-መምህራንና ለመምህራን የትምህርት አቀራረብ ዝዴዎችን ለማሻሻልና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞችን ለማቀድ ይረዳቸዋል። እያንዳንዱ የቴስት ውጤቶችም መምህራንና ወላጆች የተማሪውን አካዳሚያዊ ጥንካሬና ድክመት እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል። የልጆዎ ትምህርት ቤት ልጆዎ ምን ዓይነ ቴስት መውሰድ እንዳለበት/እንዳለባት ይነግረዎታል። ሜሪላንድ ሁለት ዓይነት ክፍለ-ግዛት አቀፍ የቴስት ፕሮግራም አላትኛ የሜሪላንድ የትምህርት ቤት ግምገማ፤ እና የሜሪላንድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግምገማ ናቸው።


## የሜሪላንድ የትምህርት ቤት ግምገማ

### የሜሪላንድ የትምህርት ቤት ግምገማ መንድን ነው?

- የሜሪላንድ የትምህርት ቤት ግምገማ (MSA) የንባብና የሂሳብ ችሎታ መለኪያ ቴስት ነው። እንደዚሁም MSA በ2008 ዓ.ም መጀመሪያ ገደማ ላይ የሳይንስ ችሎታን የሚለካ ቴስት ይሰጣል።
- MSA ማንም ልጅ ወደኋላ እንዳይቀር የሚለውን የፌደራሉን መርህ የሚያሟላ ይሆናል።
- መሰረታዊና ከፍተኛ የግንዛቤ (የእውቀት) ደረጃዎችን ይለካል።
- ቴስቱን ሰርቶ ለማጠናቀቅም፤ ተማሪዎች በቡድን ሳይሆን እያንዳንዳቸው እራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ ይደረጋል።
- ተማሪዎች ቴስቶቹን የሚወስዱት በየቀኑ በግምት ለ90 ደቂቃዎች ያክል ነው። አራት የቴስት ቀናት ይኖራሉ - ሁለቱ ቀናት ለንባብ ሁልቱ ደግሞ ለሂሳብ።
- ቴስቱ የምርጫ ጥያቄዎችንና የጽሁፍ መልስ የሚሹ ጥያቄዎችን ያካትታል።
- የቴስት ናሙና ጥያቄዎች በገጽ 12-15 ላይ ተመልክተዋል።.ተጨማሪ ጥያቄዎችም በድረ-ገጽ www.marylandpublicschools.org. ውስጥ ይገኛሉ።

## ተማሪዎች MSAን የሚወስዱት መቸ ነው?

በየዓመቱ የማርች መጀመሪያ ወቅት ላይ ከ3ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ላሉት፣ የእንግሊዝኛና፣ የሂሳብ ቴስት፣ እንደዚሁም ንባብ ለ10ኛ ክፍል ይሰጣል። እንደዚሁም ደግሞ ተማሪርዎች የጂዖሜትሪን ኮርስ ከጨረሱ በኋላ የጂዖሜትሪ ቴስት ይሰጣል። በ2008 የመጀመሪያ ወቅት ገደማ ለ3ኛ፣ 5ኛ፣ እና 8ኛ ክፍሎች ሳይንስ ይጨመራል። በክፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የሳይንስ ቴስትን ለመፈተን የፌደራል መስፈርት በሚያዘው መሰረት የሜሪላንድ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የባዮሎጂ ግምገማ የሚለውን ማሟላት ይኖርበታል። እነዚህን የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ቴስቶችን በተመለከተ በገጽ 16 ላይ ይመልከቱ።



## የልጀን የMSA ውጤት እቀበላለሁን?

አዎ። ውጤቶቹ ልጅዎ የተሰጡትን የትምህርት ዓይነቶች ምን ያክል በደንብ እንደተማረ/እንደተማረች እና አጠቃላይ በብሄራዊ ደረጃ ካሉ ልጆች ጋር ሲነጻጸር ደግሞ፣ የርሰዎ ልጅ የቱን ያክል ጥሩ እንደሰራ/ራች ያሳያሉ። የውጤት ሪፖቱም የትምህርት ቤት፣ የአካባቢ የትምህርት ሥርዓት፣ እና የክፍለ-ግዛት ትምህርታዊ የቴስት ክንዋኔዎችን ያሳያል። የMSA ውጤቶች ብቻቸውን ሊያስዩዎት የሚችሉት የልጀዎን አካዳሚያዊ ክንዋኔ ገሚሱን ብቻ ነው። ነገር ግን፣ ከልጀዎ የክፍል ስራ፣ የቤት ስራና ከሌሎች ውጤቶች ጋር ተዳምሮ በአንድ ላይ ሲታዩ፣ የ(MSA) ውጤቶች የልጀዎን አጠቃላይ ክንዋኔ በተመለከተ በጣም ጥሩ ስዕል ሊሰጡዎት ይችላሉ።

# የሜሪላንድ የትምህርት ቤት ግምገማ፤ ናሙና የቴስት ጥያቄዎች

ቀጥሎ የተመለከቱት በሜሪላንድ የትምህርት ቤት ግምገማ ተማሪዎች በሜሪላንድ የትምህርት ቤት ግምገማ ላይ የሚጠብቋቸው ዓይነት የቴስት ጥያቄ ምሳሌዎች ናቸው። ተጨማሪ የቴስት ጥያቄ ምሳሌዎችን በድረ-ገጽ www.marylandpublicschools.org. ሰፍረው ይገኛሉ።

## *ናሙና ጥያቄ - ሂሳብ ለ3ኛ ክፍል*

ትዕዛዛት: ለመልስህ የሚስማማውን ክብ በማጥቆር አመልክት።

ዳሪያ ከኪሷ ውስጥ ጥቂት ሳንቲሞች አገኘች። ቀጥሎ ያሉትን ሳንቲሞች ተመልከት።



ዳሪያ በኪሷ ውስጥ ምን ያክል ገንዘብ አገኘች?

*የተማሪው ምላሽ:*

- ○ **A** $.92
- ● **B** $1.02
- ○ **C** $.41
- ○ **D** $.42

# ናሙና ጥያቄ - ሂሳብ ለ5ኛ ክፍል

**ትዕዛዛት: ቀጥሎ ያሉትን ክ  ፍልፋዮች ተመልከትኛ**

$\frac{5}{4}$ $2\frac{1}{2}$ $\frac{13}{8}$

## ክፍል A

**ቁጥሮቹን ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ በስርዓት አስቀምጣቸውኛ**

የተማሪው ምላሽ:

$\frac{5}{4}$ $\frac{13}{8}$ $2\frac{1}{2}$

## ክፍል B

**መልስህ ትክክል መሆኑን ለማስረዳት ስለ እኩያ ክፍልፋዮች የምታውቀውን ተጠቀም፡፡ ለምትሰጠው ማስረጃ ቃላት እና/ወይም ቁጥሮች ተጠቀም፡፡**

የተማሪው ምላሽ:

መጀመሪያ 5/4ን ወደ 1 2/8 ለወጥኩትኛ ከዚያም ወደ 13/8 ወደ 1 5/8.

ከዚያ በኋላ 2 1/2 ዬ ን ወደ 2 4/8 ከዚያም በኋላ ደግሞ በቅደም-ተከተል

ስርዓት እስቀመጥኳቸውኛ 1 2/8 መጀመሪያ ላይ ይሆናል፤ ምክንያቱም 2/8

ከ5/8 ያንሳል እንደዚሁም ሁለቱም ክፍልፋዮች ከ2 ያንሳሉ፡፡

*ማስታወሻ: ተማሪዎች መልሱን በብዙ የተለያዩ መንገዶች ሊያመጡት ይችላሉ፡፡*

የሚቀጥሉት ከሜሪላንድ የትምህርት ቤት ግምገማ ላይ የተገኙ፣ ምሳሌ የንባብ ጥያቄ ዓይነቶች ናቸው:: በየክፍል ደረጃው የሚሰጠው ቴስት ሰፊ የዕውቀት ክልልን የሚሸፍኑ የተቀላቀሉ የጥያቄ ዓይነቶችን (ምርጫ፣ እና የጽሁፍ ምላሽን) ይይዛል::

## *ናሙና ጥያቄ – ንባብ ለ3ኛ ክፍል*

ትዕዛዛት: ከተሰመረበት ቃል ጋር አንድ ዓይነት ትርጉም ወይም የቀረበ የትርጉም ተመሳሳይነት ያለውን ቃል ምረጥ/ምረጪ:: ከዚያም ለመረጥከው/ለመረጥሺው መልስ ተስማሚ የሆነውን ባዶ ቦታ አጥቁር/አጥቁሪ::

<u>Sprinkle</u> ማለት ______________ ማለት ነው::

የተማሪው ምላሽ:

- ○ A ማፍላት
- ○ B መነተት
- ○ C መውቀጥ (መሸክሸክ)
- ● D መርጨት

## *ናሙና ጥያቄ – ንባብ ለ5ኛ ክፍል*

ትዕዛዛት: ከተሰመረባቸው ቃላት ወይም የቃላት ስብስቦች ጋር በትርጉም አንድ ዓይነት ወይም በቅርብ ተመሳሳይ የሆኑትን ምረጥ:: ከዚያም ለመረጥከው መልስ ተስማሚ የሆነው ባዶ ቦታ ላይ ምልክት አድርግ::

ክምሳ በኋላ ክፍሉ <u>drowsy</u> ነበር፤ እናም ሲኒማውን ለመከታተል ችግር ነበር:: <u>Drowsy</u> ማለት —

የተማሪው ምላሽ:

- ○ A ሙሉ
- ○ B የዘገየ
- ○ C ትዕግስት
- ● D እንቅልፍ የሰፈነበት

## *ናሙና ጥያቄ – ንባብ ለ8ኛ ክፍል*

*ማስታወሻ: ተማሪዎች "Arachne" እና "Damon and Pythias" የተባሉትን ታሪኮች እንዲያነቡ እናም ቀጣዮቹን ጥያቄዎች እንዲመልሱ ተጠይቀዋል::*

ትዕዛዛት: ይህን ጥያቄ አንብበህ/እንብበሽ ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ምረጭ:: ከዚያም ለመረጥከው/ለመረጥሺው መልስ በሚስማማው ባዶ ቦታ ላይ ምልክት አድርግ/እድርጊ::

Pythias ጉዳዮቹን እንዲያስተካክል በመፍቀድ፣ Dionysus — ሊሆን እንደሚችል አሳይቷል

የተማሪው ምላሽ:

- ○ A ደፋር (ጀግና)
- ● B ርኅሩኅ
- ○ C ገለልተኛ
- ○ D ውጤት አልባ

በሜሪላንድ የትምህርት ቤት ግምገማ፣ አንዳንዶቹ ጥያቄዎች የጽሁፍ ምላሽን የሚሹ ይህሆናሉ። መምህራንም እነዚህን ጥያቄዎች "የተቀናበሩ የምላሽ ዓይነቶች" ብለው ነው የሚወስዷቸው፣ ምክንያቱም፣ ተማሪዎች ተስተካክለው ከተቀነባበሩ የመልስ ምርጫዎች መካከል ከመምረጥ ፋንታ የየራሳቸውን ምላሾች አቀነባብረው ማስቀመጥ ስለሚኖርባቸው ነው። ከታች የተመለከተው ጥያቄ አጪርና በሜሪላንድ የትምህርት ቤት ግምገማ ውስጥ ከሚካተቱት የተቀነባበረ ምላሽ የሚሻ ዓይነት ጥያቄዎች መካከል አንዱ እንደምሳሌ የቀረበው ነው።

## *ናሙና ጥያቄ - ንባብ ለ8ኛ ክፍል*

*ማስታወሻ: ይህን ጥያቄ ከመመለስ በስተፊት፣ ተማሪዎች የሮዚ ሃይትስ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመልካም ዕድል ምልክት የሆነውን "ታላቁን በቅሎ" በሌላ ለመተካት ያቀረበውን ሃሳብ በመቃወም ለኤዲተሩ የተጻፉ ሁለት ደብዳቤዎችን ማንበብ ይኖርባቸዋል። ሁለቱን ደብዳቤዎች ካነበቡ በኋላ፣ በተከታታይ የተሰጡ የምርጫ ጥያቄዎችን እና የተቀነባበሩ ምላሾችን የሚሹ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ። ቀጥሎ የተመለከተው የተቀነባበረ ምላሽ የሚሻ ጥያቄ እና መልሱ ምን እንደሚመስል የሚያሳይ ነው።*

ትዕዛዛት: ለኤዲተሩ የተጻፈውን የማርግሪት ካልድዌልን ደብዳቤ አንብብ/ አንብቢ። ከዚያም የአቶን ላዝሎን ደብዳቤ አንብብ/አንብቢ።

የማርግሪት ካልድዌልን ደብዳቤ አጪር ፍሬ ሃሳብ በማጠቃለል ጻፍ/ጻፊ። በጭብጥ ማጠቃለያ ጽሁፍህ/ሽ ውስጥ ዋና ዋና ነጥቦችን ማካተትህን/ሽን አረጋግጥ/አረጋግጪ።

የተማሪው ምላሾች ሊሆኑ የሚችሉት:

ምንም እንኳን አንዳንዶች የመልካም ዕድል ምስሉን ለማስወገድ ቢፈልጉም፣ ማርግሪት ካልድዌል ከእናቷ ጋር እንደሚስማሙ ተስፋ ታደርጋለች፡፡ ከብዙ ዓመታት በፊት አንድ ተማሪ ብቅሎውን ወደውድድር እየጋለበ ሄደ፣ ቡድኑም እየተሸነፈ የነበረ ቢሆንም በመጨረሻው አሸነፈ፡፡ ይህም የማርግሪት አያት ነበር፣ እናም ያ በቅሎ የመልካም ዕድል ምስል ሆነኝኝ ለዓመታትም የመልካም ዕድል ምስል ሆኖ ቆይቷል፣ እናም እሷ ይህ ምስል እንደማይቀየር ተስፋ ታደርጋለች፣ ምክንያቱም በቅሎው በጣም ግሩም የበጎ ዕድል ምስል ሆኖ ቆይቷልና፡፡

*ማስታወሻ: ይህ ምላሽ የማርግሪት ካልድዌልን ደብዳቤ የተሟላ ግንዛቤ ያሳያል። ይሁንና፣ የተለያዩ መልሶችም ተቀባይነት ይኖራቸዋል።.*



# የሜሪላንድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግምገማ

### የሜሪላንድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግምገማዎች ምንድን ናቸው?

የሜሪላንድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግምገማዎች (HSA) የእንግሊዝኛ 1፣ የአልጀብራ/ዳታ ትንተና፣ የስነ-መንግስት፣ እና የባዮሎጂ ቴስቶች ናቸው:: ተማሪዎች እያንዳንዱን ኮርስ ከጨረሱ በኋላ እያንዳንድዱን ቴስት ይወስዳሉ:: (ይህም፣ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ያሉ ኮርሶችን የሚወስዱ የመካከለኛ ክፍል ተማሪዎችን ይጨምራል):: ቴስቱም የምርጫ ጥያቄዎችንና በጽሁፍ የሚመለሱ ጥያቄዎችን ያጠቃልላል:: ውጤቶችም ለእያንዳንዱ ተማሪ፣ ለትምህርት ቤቶች፣ ለአካባቢያዊ የትምህርት ሥርዓት፣ እና ለክፍለ-ግዛቱ ሪፖርት ይደረጋል::

### ልጄ ለመመረቅ HSA ን ማለፍ ይኖርበታልን?

የለም፣ በዚህ ወቅት አይደለም:: ሁሉም ተማሪዎች HSAን መውሰድ የሚኖርባቸው ሲሆን ማልፍ ግን ገና ግዴታ አልሆነም:: ለመመረቅ HSAን ማለፍ እንደግዴታ የሚሆንባቸው የመጀመሪያዎቹ ተማሪዎች በ2009 ዓ.ም የሚመረቁት ተማሪዎች ናቸው::

## ተማሪዎች ለHSA አፈጻጸማቸው ተጠያቂዎች ናቸውን?

አዎ:: ወላጆች እያንዳንዱን የልጆቻቸውን የቴስት ውጤቶች ይቀበላሉ:: እንደዚሁም የአካባቢ የትንህርት ሥርዓቶች፣ በመከር 2001 ወይም ከዚያ በኋላ 9ኛ ክፍል የገቡ ተማሪዎችን የእንግሊዝኛ 1፣ የአልጀብራ/ዳታት ትንተና፣ የባዮሎጂ፣ እና የሥነ-መንግስት HSA ውጤቶችን በትራንስክሪፕት ላይ እንዲያትሙ ከክፍለ-ግዛቱ ይጠበቅባቸዋል:: ስለሆነም፣ ልጅዎ የተቻለውን/ የተቻላትን ያክል ቴስቱን መሞከር ያስፈልገዋል/ ያስፈልጋታል::

## ተማሪዎች የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ድፕሎማን ለማግኘት የሜሪላንድ ተግባራዊ ቴስትርን ማለፍ ይኖርባቸዋልን?

በኦገስት 2003፣ የተግባራዊ ቴስት ፕሮግራም ይታገድ ዘንድ የሜሪላንድ ክፍለ-ግዛታዊ የትምህርት ቦርድ ወስኗል:: ድፕሎማ ለማግኘት የሜሪላንድ ተግባራዊ ቴስትን ማለፍ የግድ የሚሆንባቸው የመጨረሻዎቹ ተማሪዎች በ 2004 የሚመረቁት ብቻ ናቸው:: የተግባራዊ ቴስትን ጉዳይ የክፍለ-ግዛቲቱ የትምህርት ቦርድ እንዲቆም ስላደረገው፣ ካሁን በኋላ ትምህርት ቤቶች ማተኮር የሚኖርባቸው ተማሪዎቻቸውን ለHSA በማዘጋጀቱ ላይ ብቻ ይሆናል፡፡ HSAዎች በእርግጥ የመሰረታዊ ንባብ፣ የመጻፍ፣ እና የሒሳብ ችሎታዎችን ብቻ የሚለኩ ሆነው ከተግባራዊ ቴሰቱም በበለጠ ፈታኛና ችሎታን የሚጠይቁ ናቸው::

ልጅዎ በትምህርት ቤት ስለሚወስዳቸው ቴስቶች የሚመለከት ጥያቄ ካለዎት፣ የልጅዎን መምህር ወይም አማካሪውን/ አማካሪዋን ያነጋግሩ:: እንደዚሁም ደግሞ ለበለጠ ኢንፎርሜሽንና የናሙና ጥያቄዎችን ለመመልከት የሚመራዎትን፣ የሜሪላንድ ክፍለ-ግዛት የትምህርት ክፍል ድረ-ገጽን vwww.marylandpublicschools.org, መመልከት ይችላሉ:: ስለስኮላርሺፕና ገንዘባዊ እርዳታ ኢንፎርሜሽን ለማግኘት ደግሞ፣ የሜሪላንድ ከፍተኛ ትምህርት ኮሚሽንን ድረ-ገጽ www.mhec.state.md.us ይመልከቱ፣ እንደዚሁም ደግሞ የልጅዎን አማካሪ ያነጋግሩ::



# የሜሪላንድ ክፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግምገማ፤ ናሙና የቴስት ጥያቄዎች

## *ከአልጀብራ/ዳታ ትንተና ግምገማዎች የተቀነጨቡ*


ከዚህ በታች የተመለከቱት የቴስት ጥያቄዎች፣ በጃኑዋሪና በሜይ 2000 ለአልጀብራ/ዳታት ትንተና ከተሰጡት የቴስት ዓይነቶች የተወሰዱ ናቸው፡፡ በ2001, 2002 እና በ2003 የተሰጡ ቴስቶችን ለማየት፤ mdk12.org/mspp/high_school/look_like/ን ይጎብኙ፡፡

**ትዕዛዛት:**

ከታች የተመለከተውን ፕሮብሌም ለማቃለል፤ በመልስ መስጫው መጽሃፍ ላይ የተቀመጠውን መስመር ተጠቅም፡፡

ኪሻ ለምትሰራው የክር ስራ በሰዓት $5.50 ታስከፍላለች፡፡ እንደዚሁም ለዕያንዳንዱ የአቅርቦት ስራ $2.00 ታስከፍላለች፡፡ በጠቅላላው $35.00 ክፍያ ለማግኘት ትችል ዘንድ በአንድ ስራ ላይ ብቻ ስንት ሰዓታት መስራት ይኖርባታል?

**የተማሪ ምላሽ:**



ትዕዛዛት: ከታች ያሉትን ፕሮብሌሞች በመልስ መስጫ መጽሃፉ ላይ ስራ።

ሁለት የብስክሌት ሱቆች ለደንበኞቻቸው በልዩ ትዕዛዝ ብስክሌቶችን ይሰራሉ። ባይስክል ሲቲ፣ \$160 ሲደመር ብስክሌቱን ለመስራት የወሰደውን የእያንዳንዱን ቀን ጊዜ \$80 በመጨመር ያስከፍላል። ባይክ ታውን ደግሞ ብስክሌቱን ለመስራት ለሚወስደው ለእያንዳንዱ ቀን \$120 ያስከፍላል።

- እያንዳንዱን ሱቅ በ x ቀናት በልዩ ትዕዛዛት ለሚሰራቸው ብስክሌቶች የሚጠይቀውን የክፍያ መጠን (C) የሚያሳይ ኢኩዌሽን ጻፍ።

- በእያንዳንዱ ሱቅ ዘንድ የክፍያው መጠን አንድና ተመሳሳይ የሚሆነው ለምን ያክል ቀናት ነው? በነዚህ ቀናትስ የክፍያው መጠን ስንት ይሆናል? የመልስህን ትክክለኛነት በትክክል ለማስረገጥ ሂሳባዊ ስሌትን ተጠቀም። (ፕሮብሌሙን በግራፍ አሰራር የምታቃልል ከሆነም፣ በጽሁፍ ምላሽህ ላይ ተጨማሪ ለማድረግ በመልስ መስጫ መጽሃፉ ላይ የተሰጠውን መስመር ተጠቀም።)

- ብስክሌቶችን በትዕዛዝ ለማሰራት ባይስክል ሲቲን መጠቀም ከባይክ ታውን የበለጠ ርካሽ የሚሆነው መቸ ነው? የበለጠ ውድ የሚሆንስ መቸ ነው? የመልስህን ትክክለኛነት ለማስረገጥ ሂሳባዊ ስሌትን ተጠቀም።

የተማሪው ምላሽ:

ባይክ ሲቲ


160 + 80x=C

160 + 80(4)=480

ባይክ ታውን

120x=C

120(4)=480




ክፍያዎቹ ለ4 ቀናት በ\$480 የዋጋ ተመሳስይነት በእያንዳንዱ ሱቅ እኩል ይሆናሉ።

ረከስ የሚል ዋጋ

<u>ባይስክል ሲቲ</u>

X>4

ከአራት ቀናት በኋላ መስመሩ ዝቅ ይላል

ይበልጥ ውድ

<u>ባይክ ታውን</u>

X<4

*ማስታወሻ: ተማሪዎች መልሶቻቸውን በበርካታ የተለያዩ መንገዶች ሊያመጡት ይችላሉ።*

ትዕዛዛት: ተስማሚውን ክብ በማጥቆር መልስህን አመልክት።

ከታች ያለው ሰንጠረዥ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ አንዳንድ ኩምክናዎችን (ተንኮሎችን) መስራት የሚችሉ ውሾችን ቁጥር ያሳያል።

**የውሻ ኩምክናዎች (ተንኮሎች)**

| ኩምክና (ተንኮል) | ቁጥር (በሚሊዮን ቤት) |
|---|---|
| መቀመጥ | 5.3 |
| እጅ መጨበጥ | 3.8 |
| መንከባለል | 2.9 |
| በእግር መቆም | 1.9 |
| መዝፈን (መዘመር) | 0.8 |
| ጋዜጣ ፈልጎ ማምጣት | 0.4 |

ስቲቭ በእግራቸው ለሚቆሙት ውሾችና ለሚዘምሩት ውሾች የሚወክለውን ዋጋ በሰንጠረዡ ላይ ይደምራል። በዚህም ስሌቱ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በእግራቸው መቆም የሚችሉ ወይም የሚዘምሩ 2.7 ሚሊዮን ውሾች እንዳሉ ይደመድማል። ይህ አባባል ሥህተተኛ የዳታ አጠቃቀም የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው?

የተማሪ ምላሽ:

- ○ **A** አንድናድ ውሾች ምንም ኩምክና እንደማይሰሩ ስቲቭ ከግምት ውስጥ አላስገባም።
- ○ **B** አንዳንድ ውሾች አንድ ዓይነት ኩምክና ብቻ የሚሰሩ መሆናቸውን ስቲቭ ከግምት ውስጥ አላስገባም።
- ○ **C** ስቲቭ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ያሉ ሁሉንም ውሾች አላካተተም።
- ● **D** አንድናድ ውሾች ሁለቱንም ዓይነት ኩምክናዎች እንደሚሰሩ ስቲቭ ከግምት አላስገባም።

# የተለየ ትኩረት የሚያስፈልጋቸውን እና/ወይም የእንግሊዝኛ ችሎታቸው ውሱን የሆኑ ተማሪዎችን ስለመገምገም

አንዳንዶቹ የሜሪላንድ ተማሪዎች ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ናቸው:: ለምሳሌ፤ ልክ እንግሊዝኛ ቋንቋን ገና አዲስ መማር የጀመረ ተማሪ ሊሆን እንደሚችለው ሁሉ፤ አንድ የአካል ጉድለት ያለበት ተማሪም ለየት ያለ የትምህርት አቀራረብና የቴስት አገማገም ሁኔታ የሚያስፈልገው ሊሆን ይችላል:: ሜሪላንድ የእያንዳንዱን ተማሪ ውጤት ለማሻሻል ቁርጠኛ አቋም ያለው በመሆኑ፤ የተለየ ትኩረትና ፍላጎት ወይም ውሱን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች የእድገት መሻሻል መለካት/መመዘን በጣም አስፈላጊ ነው:: ሁሉም ተማሪዎች፤ በተቻለው መጠን ሁሉ እና፤ ሙሉ በሙሉ፤ በግዛት-አቀፍ ቴስቶች ውስጥ እንዲጠቃለሉ እናም የቴስት ውጤቶቻቸውም በሜሪላንድ የተጠያቂነት ሥርዓት አካል ይሆኑ ዘንድ ህጋዊ መብት አላቸው:: እንደዚሁም ተማሪዎች የተማሩትን በሚገባ ለማሳየት ይቻላቸው ዘንድ፤ ለትምህርት አቀራረብና ለቴስት አሰጣጥ ሁኔታዎች አቅርቦት ሁሉ ህጋዊ መብት አላቸው::

ልዩ የትምህርት አገልግሎት የሚያገኙ ተማሪዎች ሁሉንም ቴስቶች ይወስዳሉ፤ በተናጠል ሁኔታ የሚሰጣቸው የትምህርት ፕሮግራም (IEP)፤ ከዚህ ቀደም ግላዊ የችሎታ (የክህሎት) ግምገማ (IMAP) በመባል ይታወቅ የነበረውን Alt-MSAን እንደሚወስዱ የሚያዝ ካልሆነ በስተቀር:: Alt-MSA በሁል-አቀፉ (አጠቃላዩ) ሥርዓተ-ትምህርት ለማይሳተፉ ተማሪዎች የተዘጋጀ ቴስት ነው::

ትምህርታቸውን፤ በእንግሊዝኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋቸው (ESOL) ፕሮግራም የሚቀበሉ ተማሪዎች ሁሉ፤ በሁሉም ቴስቶች መሳተፍ ይኖርባቸዋል:: የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታቸው ውሱን ለሆኑ ተማሪዎችም አግባብ ያለው የክፍለ-ግዛት ቴስት አቀራረብ ሁኔታን አስመልክቶ የእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የውስን የእንግሊዝኛ ችሎታ ኮሚቴ (LEP) ውሳኔ ይሰጣል::

ለክፍለ-ግዛት የሚዘጋጁት የቴስት አቅርቦቶች በክፍል ውስጥ ከተሰጡት የትምህርት አቀራረቦች ጋር ተመሳስይ ይሆናሉ፤ ይህም ደግሞ የአካል ጉድለት ላለባቸው፤ ወይም ለ504 እቅዶች አግባብነት ላላቸው፤ ወይም የእንግሊዝኛ ችሎታቸው ውሱን ለሆኑ ተማሪዎች በIEPው አማካኝነት አጽንዖት ይሰጥባቸዋል::

ልጅዎ ልዩ ትኩረት የሚያስፈልገው፤ ወይም የእንግሊዝኛ ችሎታው ውሱን ከሆነ፤ ስለትምህርት እሰጣጥና የቴስት አሰጣጡ ሁኔታ የበለጠ ለመረዳት ይረዳዎት ዘንድ፤ ትምህርት ቤተዎን ያነጋግሩ::

# ኃላፊነት (ተጠያቂነት)

ሜሪላንድ፣ ትምህርት ቤቶችና የትምህርት ቤት ሥርዓቶች የክንዋኔ ውጤት ዳታን፣ አመርቂ የእድገት ሁኔታን፣ ሪፖርት የማድረግና፣ ትምህርት ቤቶችም የማይሻሻሉ ሆነው ሲገኙ እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት እንዳለባቸው ይገነዘባል።

## የክንዋኔ ውጤቶች ሪፖርት የሚደረጉት እንዴት ነው?

የትምህርት ቤት የክንዋኔ ውጤቶች በዓመታዊ "ሪፖርት ካርድ" (የሜሪላንድ የትምህርት ቤት የክንዋኔ ውጤት) ላይ ስለሚታተሙ፣ ወላጆች እና ኮሚዩኒቲዎች ትምህርት ቤታቸው የቱን ያክል በደንብ እየሰራ እንደሆነ ሊያውቁና ሊገነዘቡ ይችላሉ። ይህ ሪፖርትም በድረ-ገጽwww.mdreportcard.org. ላይ ይገኛል። ሁሉም ተማሪዎች ጥሩ መሻሻል እያደረጉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ፣ ክፍለ-ግዛቱ፣ የትምህርት ቤት ሥርዓቱ፣ እና የትምህርት ቤት ውጤቶች በብሄር/ ጎሳ፣ በጾታ፣ በአካለ-ጎደሎነት፣ በድህነት ደረጃ፣ በስደተኛነት ደረጃ፣ እንደዚሁም በውሱን የእንግሊዝኛ ችሎታ ደረጃ ሪፖርት ይደረጋሉ። (የየተማሪው የግል ውጤቶች ግን ለህዝብ ይፋ አይደረጉም። ኢንፎርሜሽኑ ለርሰዎና ለልጆዎ መምህራን ብቻ ነው።)

## ዕድገትና መሻሻል የሚያደርጉ ትምህርት ቤቶች ይሸለማሉን?

ትምህርት ቤቶች መሻሻል ካሳዩ የገንዘብ ሽልማትና እውቅና ሊያገኙ ይችላሉ።

## አንድ ትምህርት ቤት ምንም እድገት የማያሳይ ከሆነ ምን ይደረጋል?

ሜሪላንድ፣ ለተማሪዎች እድገትና መሻሻል ዓመታዊ ግቦችን አስቀምጧል። ትምህርት ቤቶችም፣ በሁሉም ንዑስ የተማሪዎች ቡድኖቻቸው አኳያ፣ በቂና አመርቂ ዓመታዊ እድገትና መሻሻል (AYP) ያደርጉ ዘንድ፣ ሁሉንም ግቦቻቸውን ማሳካት ይኖርባቸዋል። ማንም ልጅ ወደኋላ አይቀርም የሚለው የፌደራል ድንጋጌ፣ ሜሪላንድ (AYP)ን በመከታተልና በመቆጣጠር፣ ውጤቶችንም ለወላጆች ሪፖርት በማድረግ፣ ተምህርት ቤትችም በበቂው ሁኔታ እየሰሩና እየተሻሻሉ ባልሆኑበት ሁኔታ እርምጃ በመውሰድ እንዲታጠናክረው ይጠበቅባታል።

- ለሁለት ተከታታይ ዓመታት ያክል አመርቂ ዓመታዊ እድገት (AYP) የማያደርግ ትምህርት ቤት፣ የክፍለ-ግዛት ትምህርት ቤት ማሻሻያ ዓመት 1 ተብሎ ይያዛል። ትምህርት ቤቱም በተማሪዎች የውጤት ዕድገትና መሻሻል አኳያ የዕድገት ዕቅዱን መመርመር ይኖርበታል። ትምህርት ቤቱ ክፍተኛ የድህነት ደረጃ በሚባለው በፌደራል ርዕስ I ፕሮግራም ደረጃ

የሚሳተፍ ከሆነ፣ ወላጆች ልጆቻቸውን በአካባቢያቸው ወደሚገኛና ከፍተኛ ውጤት ወደሚያስገኛ ትምህርት ቤት እንዲያዛውሩ እድሉን ሊሰጣቸው ይገባል።

- ትምህርት ቤቱ ለሦሥተኛ ዓመትም ምንም ዕድገትና መሻሻል (AYP) የማያስያ ከሆነ፣ ወደ የክፍለ-ግዛት የትምህርት ቤት ማሻሻያ ፕሮግራም ዓመት 2 ይተላለፋል፡፡ ትምህርት ቤቱ የዕድገትና መሻሻል ዕቅዱን መከተሉን መቀጠል ይኖርበታል። ትምህርት ቤቱ ርዕስ I ትምህርት ቤት ከሆነ፣ ለምሳሌ በኢኮኖሚያቸው በጣም የተጎዱ የሆኑ ተማሪዎችን በግል እንደማስጠናት የመሳሰሉትን ተጨማሪ አገልግሎቶችን መስጠት ይኖርበታል። ነጻ ወይም ባለ ቅናሽ ዋጋ ምግብ የማግኘት ዕድል የተሰጣቸው ተማሪዎች፣ በኢኮኖሚ የተጎዱ ከሚባሉት መካከል ናቸው።

- ትምህርት ቤቱ ለአራተኛ ዓመትም ዕድገትና መሻሻል (AYP) ካላሳየ፣ ወደ እርምት እርምጃ እንዲተላለፍ የሚደረግ ሲሆን፣ የትምህርት ቤት ሥርዓቱም ትምህርት ቤቱን ለማሻሻል የሚረዳ ቁርጠኛ ዕርምጃ መውሰድ ይኖርበታል። እነዚህ እርምጃዎችም፣ የትምህርት ቤት ስታፍ መቀየር (በሌሎች መተካት)ን፣ አዲስ ሥርዓተ-ትምህርት በስራ ላይ ማዋልን፣ ወይም የትምህርት ቤት ዓመት ማራዘምን ያጠቃልላሉ።

- ትምህርት ቤቱ ለአምስተኛ ዓመትም ዕድገትና መሻሻል (AYP) የማያሳይ ከሆነ፣ ወደመልሶ ማቋቋምና መዋቅር ማስተካከል ይተላለፋል። መልሶ ማቋቋምና መዋቅር ማስተካከልም የትምህርት ቤቱ እንቅስቃሴ በክፍለ-ግዛቱ ወይም በአካባቢው የትምህርት ቤት ሥርዓት ኃላፊነት ስር እንዲውል ማድረግንና ሌሎች እርምጃዎችን ሊጨምር ይችላል።

- እንድ ትምህርት ቤት ከላይ የተዘረዘሩት እርምጃዎች እንዲወሰዱበት የሚያስፈልገው ከሆነ፣ ወላጆች ይህንኑ እንዲያውቁት ይደረጋል። ትምህርት ቤቶች ለሁለት ዓመታት አመርቂ ዕድገትና መሻሻል (AYP) ካደረጉ፣ ከክፍለ-ግዝት የትምህርት ቤት ማሻሻያ ዕቅድ ውስጥ ይወጣሉ።

የክፍለ-ግዛት የትምህርት ቤት ማሻሻያ፣ ለዕድገት ዕድል ከፋች መሆኑ መታወቅ አለበት። እንድ ትምህርት ቤት እድገትና መሻሻል እንደሚያስፈልገው ታወቀ ማለትም፣ ትምህርት ቤቱ መጥፎ ትምህርት ቤት ነው ማለት አይደለም። በእርግጥ፣ ትምህርት ቤቱ በአማካይ ደረጃ በጣም ጥሩ እየሰራ ያለ፣ ነገር ግን አንድ ወይም ከዚያ በላይ ለሚሆኑ ንዑስ ቡድኖች መሻሻል የበለጠ መስራት የሚኖርበት ስለሆነ ብቻ ነው። መሻሻል ስለሚገባቸው ትምህርት ቤቶች ዝርዝር፣ የድረ-ገጽ www.mdreportcard.orgን ይጎብኙ።



# የቤተሰብ ተሳትፎ

የቤተሰብ ተስትፎ በተማሪ ውጤት መሻሻል ላይ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያለው መሆኑን በመገንዘብ፣ ሜሪላንድ የቤተሰብ ተሳትፎ ፖሊሲን በስራ ላይ አውሏል። በመከር 2003፣ የትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ የሆኑት Nancy Grasmick፣ ክፍለ-ግዛቱ ያለማቸውን ግቦች ለመምታት ወላጆች በትምህርት ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ተሳትፎ በማድረግ ሊያግዙ የሚችሉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፣ (ገጽ 5 ይመልከቱ)፣ የሜሪላንድ የወላጆች እማካሪ ካውንስል (M-PAC)ን አቋቁመዋል። M-PAC የወላጆችን የተሳትፎ ጉዳይ በተመለከተ ለክፍለ-ግዛቱ የትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪና ለግዛቱ የትምህርት ቦርድ የአማካሪነት ሚና የሚጫወት 140 ወላጆችና ደጋፊዎች የተሰባሰቡበት የአማካሪዎች ቡድን ነው። M-Pacን የሚመለከት የበለጠ ኢንፎርሜሽን በድረ-ገጽ www.marlandpublicschools.org ላይ ያገኛሉ።

የሜሪላንድ ትምህርት ቤቶች ወላጆችንና ህጋዊ ሞግዚቶችን (አሳዳጊዎችን) በየትምህርት ቤቶቻቸው በደስታ ይቀበላሉ፣ ጥያቄዎችን እንዲጠይቁ ያበረታታሉ፣ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደትም እንዲሳተፉ ያበረታታሉ። በልጅዎ ትምህርት ቤት ውስጥ፣ ቤተሰቦችና የትምህርት ባለሙያዎች እንዴት እንደሚገናኙና እንደሚግባቡ እናም እንዴት አብረው እንደሚሰሩ ለመረዳት ቀጥሎ ያሉትን ጠቋሚ ምልክቶች ያስተውሉ።

### ትምህርት ቤቶችና ቤተሰቦች ዘውትር ይገናኛሉ።

- ትምህርት ቤቶች፣ ቤተሰቦች ልጆቻቸው እንዲማሩ ለማገዝ የሚያስችሏቸውን ምክሮች ያካተቱ የዜና መጽሄቶችን ያሳትማሉ።

- በትምህርት ቤት የሚካሄዱ ፕሮግራሞችን አስመልክተው ትምህርት ቤቶች ከቤተሰቦች ጋር ይነጋገራሉ።

- ወላጆች የልጆቻቸውን መምህራን እንዴትና መቸ እንደሚያነጋግሩ ይገነዘባሉ።

## ተማሪዎች በደንብ እንዲማሩ ወላጆች ሚና ይጫወታሉ።

- መምህራን ወላጆች ልጆቻቸው የቤት ስራዎቻቸውን ሲሰሩ እንዴት መርዳት እንዳለባቸው እንዲገነዘቡ ይረዳሉ።

- ወላጆች ለልጃቸው የሚሆን ግብን በማቀዱ ሂደት ይሳተፋሉ።

## ወላጆች በትምህርት ቤት ጥሩ አቀባበል ይደረግላቸዋል፤ የሚያደርጉት እገዛም ይወደሳል።

- ወላጆችና የቤተሰብ አባላት በትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ላይ እንዲሳተፉ ትምህርት ቤቶች ያበረታታሉ።

- ወላጆች ለትምህርት ቤት በፈቃደኛነት የማገልገልን ዕድል ይገነዘባሉ።

## ወላጆች የልጆቻቸውን ጉዳይ በሚነካ ማንኛውም ውሳኔ ላይ ይካተታሉ።

- ትምህርት ቤቱ ውሳኔ ላማሳለፍና ችግሮችን ለምፍታት ግልጽ የሆነ ሂደት አለው።

- ወላጆች የትምህርት ቤት ፖሊሲዎችንና የተማሪዎችንም ሆነ የትምህርት ቤት የስራ ውጤትን በተመለከተ፤ ወቅታዊ ኢንፎርሜሽኖችን የማግኘት እድል አላቸው።

- አስተማሪዎችና አስተዳዳሪዎች፤ ወላጆች የልጃቸውን ጉዳይ በሚመለከቱ (ለምሳሌ፤ ኮርስ የመምረጥን፤ የወደፊት የሙያ አቅጣጫን ማመላከትን በሚመለከቱ) የውሳኔ አሰጣጣ ሂደቶች ላይ እንዲሳተፉ ያበረታታሉ።

- የወላጅ ተወካዮች በትምህርት ቤት የዕድገት ቡድን ውስጥ ይካተታሉ።

ትምህርት ቤቶችን ለማሻሻል ቤተሰቦችና ትምህርት ቤቶች በጋራ ከሚሰሩባቸው መንገዶች ጥቂቶቹ እነዚህ ናቸው። በጉዳዩ ላይ እንዴት ይበልጥ መሳተፍ እንደሚችሉ የልጅዎን አስተማሪ ወም ርዕሰ-መምህር መጠየቅ ይችላሉ። ቤተሰቦችና ትምህርት ቤቶች በጋራ ሲሰሩ፤ እያንዳንዱ ሰው ያሸንፋል።



# ጥሩ ውጤትን ስለማበረታታት

ልጅዎ በትምህርቱም ሆነ የወደፊት ህይወቱ እንዲሳካለት/እንዲሳካላት ይፈልጋሉ። ስኬታማ እንዲሆን/እንዲትሆንም ለማበረታታት ብዙ መንገዶች አሉ። ቀጥሎ ያሉት፣ ልጅዎ በትምህርቱ/በትምህርቷ የበለጠ ጎበዝ እንዲሆን/እንድትሆን እርስዎ እገዛ ሊያደርጉ ከሚችሉባቸው መንገዶች ጥቂቶቹ ናቸው።

- ከልጅዎ ከፍ ያለ (የላቀ) ስኬታማ ውጤት ይጠብቁ። ቅድሚያ ትኩረቱን/ትኩረቷን ለትምህርቱ/ቷ እንዲያደርግ/እንድታደርግ ያድርጉ።

- ስለልጅዎ የትምህርት ዕድገትና መሻሻል እናም እርሰዎስ ልጅዎ የበለጠ መሻሻል እንዲያደርግ/እንዲታደርግ ምን ማድረግ እንደሚገባዎት ዘውትር ከልጅዎ አስተማሪዎች ጋር ይወያዩ።

- የልጅዎን የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ምርጫን ለማቀድ፣ ልጅዎ ገና በመካከለኛ ክፍል እያለ/እያለች ከልጅዎ አማካሪ ጋር ተገናኛተው ይነጋገሩ።

- ከልጅዎ ጋር ለማንበብና ለመነጋገር በየቀኑ ቢያንስ 15 ደቂቃዎችን ይመድቡ። (ስለቤተሰብ ተግባሮች የተሰጠውን የአስተያየቶች ዝርዝርና

ለቤተስብ የሚሆኑ የየዕለት ክንዋኔ ተመክሮዎችን በተመለከተ፤ *ለቤተሰበዎ 15 ደቂቃዎች ይውሰዱ* የሚለውን በድረ-ገጽ www.marylandpublicschools.org/family_literacy/take15.htm.) ላይ ይመልከቱ፡፡

- ለልጅዎ ማጥኛ በጣም ጸጥተኛ ቦታ ያዘጋጁ፡፡
- ልጅዎን በቤት ስራው/በቤት ስራዋ ይርዱ፡፡
- ልጅዎ በትምህርት ቤት ምን እያደረገ/ች (እየተማረ/ች) እንደሆነ ለማወቅ ይጣሩ፡፡
- ልጅዎ ቴሌቪዥን ለማየት የሚጠቀምበትን/የምትጠቀምበትን ጊዜ በገደብ ያድርጉ፤ እንደዚሁም ከቴሌቪዥን ስለአየው/ስለአየችው ነገር ያወያዩት/ያወያዩአት፡፡
- ልጅዎ በቪድዮ ጨዋታ ላይ እና በኢንተርኔት ላይ የሚያጠፋውን/የምታጠፋውን ጊዜ ይቆጣጠሩ፡፡
- የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎችን ለማገዝና ሌሎች ወላጆችም እንዲሳተፉ ለማበረታታ ፈቃደኛነተዎትን ያሳዩ፡፡
- ልጅዎ ችሎታን የሚፈትኑ ኮርሶችን እንዲወስድ/እንድትወስድ ያበረታቱ፡፡
- ልጅዎ በመካከለኛ ክፍል ወይም በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሆነ/ከሆነች፤ ስለ ድሕረ-ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ዕድሎች ከልጅዎ አማካሪ ጋር ለመነጋገር ቀጠሮ ይያዙ፡፡

ከልጅዎ ጋር ለማንበብና ለመነጋገር ለእያንዳንዱ ቀን ቢያንስ 15 ደቂቃዎችን መድበው ያስቀምጡ

# ለበለጠ ኢንፎርሜሽን

የተማሪ ወይም የትምህርት ቤት የስራ እንቅስቃሴ ውጤትን በተመለከተ ጥያቄ ካለዎት፤ ጥያቄዎን ለመጀመር ጥሩው መነሻ ቦታ የሚሆነው፤ የልጅዎ አስተማሪ፤ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ-መምህር፤ ወይም አማካሪ ነው:: የአካባቢዎ የትምህርት ሥርዓትም ሌላው ጥሩው የኢንፎርሜሽን ምንጭ ነው:: እንደዚሁም የህዝብ ቤተ-መጽሐፍተዎን (የህዝብ ላይብራሪን)ም አይዘንጉት! ወደ ድረ-ገጾች (ዌብ) ለመግባትና ኢፎርሜሽን ለማፈላለግም፤ የቤተ-መጽሐፍቱን ኮምፒዩተር መጠቀም ይችላሉ:: ስለኢንፎርሜሽን አፈላለጉም የቤተ-መጽሐፍቱ የስታፍ አባላት ሊረዱዎት ይችላሉ:: ቀጥሎ የተዘረዘሩት ድርጅቶች፤ ስለተማሪ የክንዋኔ ውጤቶችና ስለትምህርት ቤቶች ዕድገትና መሻሻል የበለጠ እንዲያውቁ ሊረዱዎት ይችላሉ::

**የሜሪላንድ ክፍለ-ግዛት የትምህርት ክፍል**
**MARYLAND STATE DEPARTMENT OF EDUCATION**
200 West Baltimore Street
Baltimore, MD 21201
**ስልክ**: 410-767-0600 ***ወይም*** 888-246-0016
**ፋክስ**: 410-333-2275
TTY/TDD 410-333-3045

**www.marylandpublicschools.org**
*ለጋዜጣዊ መግለጫዎችና የፕሮግራም ኢንፎርሜሽን*

**www.mdk12.org**
*የትምህርት አቀራረብን፤ የትምህርት ቤት ዕድገትና መሻሻልን የሚመለከተውን ቡድን፤*
*እና ሌሎችንም ለሚመለከት ኢንፎርሜሽን*

**www.mdreportcard.org**
*ስለትምህርት ቤቶች የስራ ክንዋኔ ሂደት በሚመለከት*

**ሜሪላንድ PTA**
**MARYLAND PTA**
5 Central Avenue
Glen Burnie, MD 21061
**ስልክ**: 410-760-6221 ***ወይም*** 1-800-707-7972
**ፋክስ**: 410-760-6344
**www.mdpta.org**

**የዩ.ኤስ የትምህርት ክፍል**
**U.S. DEPARTMENT OF EDUCATION**
400 Maryland Avenue, SW
Washington, DC 20202
**ስልክ**: 1-800-USA-LEARN
**ፋክስ**: 202-401-0689
TTY/TDD 1-800-437-0833

**www.ed.gov**
*ለአጠቃላይ ኢንፎርሜሽን፡*

**www.nochildleftbehind.org**
*ማንም ልጅ ወደኋላ አይቀርም የሚለውን ድንጋጌ ለሚመለከት ኢንፎርሜሽን፡፡*

**ሜሪላንድ የክፍተኛ ትምህርት ኮሚሽን**
**MARYLAND HIGHER EDUCATION COMMISSION**
*ኮሌጆችን፤ የገንዘባዊ እርዳታንና ስኮላርሺፕን ለሚመለከት ኢንፎርሜሽን፡*

839 Bestgate Road, Suite 400
Annapolis, Maryland 21401
**ስልክ**: 410-260-4500 ***ወይም*** 1-800-974-0203
*ለክልላዊ የኢንፎርሜሽን ማጠያየቂያ*

**ስልክ**: 410-260-4565 ***ወይም*** 1-800-974-1024
*ገንዘባዊ እርዳታን ለማጠያየቅ*

**ፋክስ**: 410-260-3200
TTY 800-735-2258
**www.mhec.state.md.us**



# እንዴት እየሰራን ነን?

**የሜሪላንድን ግቦች ለህዝብ ትምህርት፤ ትምህርት ቤቶችን ለማሻሻልና ለማሳደግ የሚደረጉ ጥረቶችን፤ እናም ወላጆችስ ልጆቻቸውንና ትምህርት ቤቶቻቸውን ለማሻሻልና ለማስደግ ምን ማድረግ ይችላሉ፤ የሚሉትን ለመረዳትና ለመግንዘብ ይህ የህትመት ውጤት የቱን ያክል እየረዳዎት እንደሆነ ከርሰዎ ለመስማት እንፈልጋለን፡፡ እባከዎ ቀጥሎ የተመለከተውን መጠይቅ ለመሙላት ጥቂት ጊዜዎን ይውሰዱ፡፡**

**1.** በዚህ ህትመት ላይ የሰፈሩትን ነገሮች ተረድተዋቸዋልኛ?

___ አዎ ___ የለም አልተረዳኋቸውም ___ አንዳንዶቹን ከሌሎቹ የተሻለ ተረድቻቸዋልሁ፡፡

እባከዎ ምርጫዎን ያብራሩት፡፡

**2.** እርሰዎ ጉዳየ ብለው የሚጨነቁላቸውንና የሚያሳሱቡዎትን የሚመለከቱ ጉዳዮችን አንስተናልን?

___አዎ ___የለም እላነሳችሁም ___ ከአንዳንዶቹ የበለጠ ለሎቹ በጣም አስባለሁ፡፡

እባከዎ ምርጫዎን ያብራሩት፡፡

**3.** በእያንዳንዱ ርዕሰ-ጋዳይ ላይ የሚገባውን ያክል ዝርዝር ሁኔታ በበቂው አቅርበናልን?

___ አዎ ___ የለም፤ ዝርዝሩ *በጣም በዝቷል* ___ የለም፤ ዝርዝሩ *በቂ አይደለም*፡፡

እባከዎ ምርጫዎን ያብራሩት፡፡

**4.** ተጨማሪ አስተያየት

**እንዴት እየሰራን እንደሆነ እንድናውቅ የሚረዳንን ምላሽዎን ለመስጠት ጊዜዎን ስለውዱ በጣም እናመሰግናለን፡፡ እባከዎ ይህን ገጽ ቆኗጠው በፋክስ ቁጥኗ** 410-333-2275 **ወይም ደግሞ፤** Maryland State Department of Education, Communications and Strategic Planning Office, 200 West Baltimore Street, Baltimore, Maryland 21201-2595 **ብለው በፖስታ ይላኩት፡፡**

# የሜሪላንድ ግዛት የትምህርት ክፍል
# የኢንፎርሜሽን መጠየቂያ

ቀጥሎ የተዘረዘሩት ነገሮች በድረ-ገጽ www.marylandpublicschools.org ላይ ይገኛሉ።
በወረቀት ላይ የታተሙ ቅጂዎቹን ለመጠየቅ ከፈለጉ፣ ይህን ቅጽ ይጠቀሙ።

_______ *ሜሪላንድ የትምህርት ቤት የስራ ክንውን ሪፖርት* (የክፍለ-ግዛትና የአካባቢ የትምህርት ሥርዓት ዓመታዊ ሪፖርት)

_______ *የኢንፎርሜሽን (የመረጃ) ዝርዝር መጽሀፍ* (የህዝብ ትምህርት ስታቲስቲካዊ መረጃ)

*የኢንፎርሜሽን (የመረጃ) ዝርዝር ወረቀቶች* (ተከታታ ባለአንድ ገጽ የኢንፎርሜሽን ወረቀቶች)

______ የመሪላንድ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግምገማዎ
______ ችወደላቀ ደረጃ የመሸጋገሪያ ድልድይ ለህዝብ ትምህርት ቤቶች ድንጋጌ
______ በመሻሻል ላይ ያሉ፣ በእርምት እርምጃ ላይ ያሉ፣ በመልሶ ግንባታና መዋቅር መስተካከል ላይ ያሉ ትምህርት ቤቶች።

_______ * *ቴስቲንግ (ግምገማ) በሜሪላንድ: የወላጅ መምሪያ ስለ ሜሪላንድ የትምህርት ቤት ግምገማ።*

_______ * *የሜሪላንድ የከፍተኛ ሁለተ: ደረጃ ትምህርት ቤት ግምገማኛ ከክፍለ-ግዛቱ የትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ ለወላጆች የተላለፈ መልዕክት።*

_______ * *የተሳካ ውጤት ከምንም በላይ ስለመሆኑ የወላጆች መምሪያ* (የዚህን ህትመት ተጨማሪ ቅጂዎች ለመጠየቅ)።

* *ይህ ህትመት በተወሰኑ የተመረጡ የውጪ ቋንቋዎች ተዘጋጅቶ ይገኛልኛ እባከዎ የሚፈልጉትን ቋንቋ ለይተው ያሳውቁ።*

ስመዎ: ______________________________________________

እድራሻ: ______________________________________________

የቀን ስልክ: ______________________________________________

ይላክ ለ: The Maryland State Department of Education
Communications and Strategic Planning Office
200 West Baltimore Street
Baltimore, Maryland 21201-2595

ወይም ፋክስ ለ: 410-333-2275